# ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ሱዳንን ይጎበኛሉ

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ለሶስት ቀን ያህል ሱዳንን ይጎበኛሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ ባለስልጣናትን ያቀፈ የልኡካን ቡድንን መርተው ማክሰኞ ነሃሴ 9 ቀን 2017 ዓ.ም ወደ ካርቱም ያቀናሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሱዳን ጉብኝት የሚያደርጉት፣ የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ኦማር ሃሰን አል-በሽር ባደረጉላቸው ግብዣ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፕሬዝዳንት አል-በሽር ጋር በሁለቱ አገሮች፣ በአካባቢያዊና አለምአቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ጉብኝቱ የኢትዮ-ሱዳንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡

ሁለቱ አገሮች በሰላምና ጸጥታ፣ በንግድና ኢኮኖሚ ትብብር፣ በመንገድ ትስስር፣ በደን ልማትና እንክብካቤ እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች በአጠቃላይ ስምንት በሚሆኑ የተለያዩ የሁለትዮሽ ስምምነቶችን መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

*ቃል-አቀባይ ጽ/ቤት*

*ነሀሴ 8 ቀን 2009 ዓ.ም*